# ሚዲያ ከሕዝብ ይልቅ
# ግለሰብን ሲወግን !!

በአበበ አረዳ

በመሠረታዊው ጽንሰ-ሃሳብ ሜዲያ የሕዝብ ዓይንና ጆሮ ሆኖ ነው የሚ
መሠረተው ሲባል እንሰማለን ። ነገር ግን በኛ በኢትዮዮጵያዊያን ዘንድ
ሜዲያ ሕዝባዊ ስሜቱ በተገላቢጦሽነት የግለሰቦች ነውር መደበቂያ ወይም
የፖለቲካውን ስውር ደባ መፈጸሚያ መሣሪያ ሆኖ እያየነው ነው ። በሰለጠ
ኑት ዓለማት ግን ሜዲያው ቢያንስ 60/70 ፐርሰንት ያህሉ የሕዝብ ጆሮና
ዓይን ሆኖ እያገለገለ መሆኑን ብዙዎቻችን የምናምነው ነው ። ካሁን ቀደም
ይህንን በመሳሰለ ጉዳይ ሜዲያዎች ጎራ ለይተው ፣ አንዳንድ ጸሐፊዎችም
በሜዲያዎች ያላቸውን ቅሬታ በተለያየ ጊዜ አውጥተው አንብቤያለሁ ።

በኢትዮጵያ ሀገራችንም ለጥቂት ግለሰባዊ ቡድኖች ገፈፉና ብዙሃኑን ለመ
ጨቆን ሲባል ወያኔውና አበሮቹ በዚህ ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን የሕዝቡን
መገናኛ ብዙሃን በራሳቸው ቁጥጥር ሥር አድርገው ፣ ከገዢው ፕሮፓጋንዳ
በስተቀር አንዳች የሚሰማው ነገር እንደሌለው በሰፊውና በጥልቅ ተገንዝቤ
ያለሁ ። ሕዝቡ በዓለማችን ውስጥ ምን እየተሠራ እንዳለ አያውቅም ። መገ
ናኛ ብየሃንን ማፈን እንደ ጀግንነት ተቆጥሮ በመለስ ዜናዊ ሲፎከር የነበረበ
ትንም ጊዜ አንዘነጋውም ። ከሁሉ በላይ የሚያሳዝነው ግን በዚህ ሠለጠነ እየ
ተባለ በሚነገርበት ሀገረ አውሮፓና አሜሪካ ሚዲያዎቹ የሚጠበቅባቸውን
በአግባቡ ከማሟላት ይልቅ ፣ በኢትዮጵያዊነት ስም ያቋቋሙትን ሜዲያ ለግ
ለሰቦች ክብር መጠበቂያ ፣ ነውር መሸፋፈኛ ማድረጋቸው ነው ።

ዕውነት ለመናገር አንድ ሜዲያ ትችት ወይም ዘለፋ ወይም አንድ የሆነ
ቅዋሜ ቢደርስበት ፣ በሜዲያው ላይ አመክንዮ የሆነውን ጉዳይ ሜዲያው
ሳይሸሽግ በግልጽ ማውጣትና ፣ ለቀረበውም ሂስ ሆነ ተቃውሞ በቂ መልስ
መስጠት ይገባዋል የሚል ዕምነት አለኝ ። ያ ካልሆነ ግን ሜዲያውን በሕ
ዝብ ስም ለማስመሰል ማቅረብ ወይም የሕዝብ ነው ብሎ ማስተዋወቅ ከማ
ታለያነት አልፎ ሕዝባዊ ወገናዊነት አለው ብሎ የሚያምን የለም ።

ብቻ አንድ ጊዜ በመጥፎ ሽክርክሪት ውስጥ ገብተናልና ፣ ሐሰቱንም ተለ
ማምደነዋልና ፣ ሕዝቡንም እንደሞኝ ቆጥረነዋልና እኛን የሚያጋልጠን ጊዜ
አይመጣም ተብሎ ከሆነ ፣ በኔ በኩል እንዲህ ዓይነቶቹ ሜዲያዎች በሰፊው
የሚጋለጡበት ጊዜ ስለደረሰ ፣ ኢትዮጵያዊያን ወገኖች ነገሮችን ፍርጥርጥ
አድርገን በማውጣት ሕዝባዊ ሜዲያን በመደገፍ ፣ አምታቾቹንም ልናጋልጥ
ይገባናል የሚል ዕምነት አለኝ ።

ይህን ጽሁፍ ያቀረብሁት ያለምክንያት አይደለም ። በቂ ምክንያትና ለም
ክንያቶቼም በቂ ማስረጃ ያለኝ ነኝ ። ለአንዲት ቀን መሰናክል ውስጥ ሳልገባ
ያቺን ያሳደገችኝንና ለቁምነገር ያበቃችኝን ኢትዮጵያን ለማዳን ከወገኖች
ጋር እየታገልሁላት ፣ የምችለውን ሁሉ ባለኝ ሙያና ዕውቀት ልሠራ የሚገ
ባኝን እየሠራሁ ነኝ ። ሆኖም በዚህ የመከራ ዘመን ጊዜ ሰጠን ፣ ጊዜው ደል
ቶናልና የፈለግነውን ብናደርግ ማንም አይዳኘንም ብለው በልባቸው ያደረ
ባቸውን ወንጀል በመመካት ብቻ ኢትዮጵያዊ ወገንን የሚያሠቃዩትን ግን
እስከ መጨረሻው የምፋለማቸው በመሆኑ ፣ ባለፉት ሳምንታት የልጄን የሳ
ምራዊት አበበን ጉዳይ ለሜዲያዎች አብቅቼ እንደነበረ የሚታወስ ነው ።

ምንም አንዳንድ አስመሳይ ሜዲያዎች በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም ተቋቁ
መው የግል ኢንተረስታቸውን ብቻ ቢመለከቱም ፣ አንዳንድ ዕውነታን እየ
ተከተሉ ያሉ ሜዲያዎች የሕዝብ ጆሮና ዓይን በመሆን የቀረበላቸውን የሕ
ዝብ ጥያቄ በዌብ ሳይታቸው ላይ ለማሳየት መሞከራቸው እሙን ነው ።
እኔ ያንን ጽሁፍ ያቀረብሁት በዕውነትና ሕግን ተመርኩዤ ፣ እንዲሁም ከደ
ረሰው ዓይን ያወጣ ግፍ የተነሳ ነው ። ይህ የደረሰው ግፍ ከባድና አሰቃቂ
ከመሆኑም በላይ በዝና ብቻ ከተካበው ነገር ግን ሥነ-ምግባር ካነሰው ግለሰብ
በልጄ ላይ የተሠነዘረ ጥቃት ከመሆኑ የተነሣ እንጂ ፣ አንዳች መሠረት በሌ
ለው ነገር ተነሳስቼ የገለጽሁት እንዳልሆነ ማንኛውም የሰው ልጅ በሕሊናው

ገምቶ ፍርድ የሚሰጥበት መሆኑን በማመን ነው ። እኔ በሕግ ሙያና በተለ
ያዩ አኩሪ ሙያዎቼ ሀገሬን ያገለገልሁ ፣ ሕግና ሥነምግባር ገንዘቦቼ የሆኑ ፣
ቢያስፈልግ እጅግ በርካታ ኢትዮጵያዊያን እኔነቴን ሊገልጹልኝ የሚችሉ
የበርካታ ቤተሰቦች ኃላፊነት ያለኝመሆኔን ወደፊት ትደርሱበታላችሁና ብዙ
አላወራም ።

ይህ የገለጽሁት የሳምራዊት ጉዳይ ምን ያህል ዕውነት እንደሆነና ጠበቃ
ተብዬው የፈጸመውንም ግፍ ፣ በሰውም የሕግ ሚዛን ሆነ በአግዚአብሔር
መፈረዱና ለያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በግልጽ የሚቀርብ መሆኑን አልጠራጠ
ርም ። ያቀረብሁትን ጽሁፍ የተመለከቱ የተለያዩ የሚዲያው ኃላፊዎች
ወይም ጉዳዩ ይመለከተናል ያሉ በኢሜል ሃዘናቸውን ሲገልጹ ለሕዝብ ዓይ
ኖችና ጆሮዎች እንዲቀርብ ግን አላደረጉም ።

አሁን ጥያቄው እንደ ቀበሌ ዳኛ የሕዝብን ጉዳይ ከፋይላችሁ አስቀምጣ
ችሁ ለምንድነው ለሕዝብ ይፋ ያላወጣችሁት ? የሚል ነው ። ይህ ጠበቃ
ተብዬው ምን ሠርቶ ነው ያን ያህል ገንዘብ ወስዶ ጉዳዩን ያቋረጠው ? ጉዳ
ዩን ለማቋረጥስ ትክክለኛውና አመርቂ ማስረጃው ምንድነው ? በሶስት ወር
ጊዜ ውስጥ የሥራ ፈቃዷንና መኖሪያዋን አሰጣታለሁ ፣ የሷ ጉዳይ የበሰለ
ነው ብሎ 4086 ዶላር ከወሰደ በኋላ ፣ ለስምንት ወራት ጉዳዩ ላይ ተኝቶ ፣
ያላንዳች ምክንያት ከዛሬ ጀምሮ ጠበቃሽ አይደለሁም ብሎ ሥራውን ለማ
ቆም ያበቃው መነሻው ምክንያት ምንድር ነው ? በእርግጥ በመጀመሪያው
መልዕክቴ ገልጬ እንደነበረ የምታስታውሱት ነው ። በአንዲት ሴት ልጅ
ላይ ያውም ኢትዮጵያዊ ወገኑ ላይ ይህን መሰል ግፍ ለምን ፈጸመባት
ብሎ ለሜዲያ መግለጽ ነውር ሆኖ ነው ? ወይስ ግለሰቡ ለሜዲያው ያለው
መቀራርብ ከኢትዮጵያዊቷ ልጅ ሥቃይ ስለበለጠ ? ለነገሩ የጠበቃውን
ማንነትና በሱ ጉራ ሥር የወደቁትን ለሰብዓዊ ኅሊናቸው ያልተገዙትን የሜ
ዲያ ባለ እንዱስትሪዎችን ተግባራት ሌሎችም ኢትዮጵያዊያን ጠንቅቀው
ስለሚያውቁት እኔም ስለማውቀው ፣ እዚህ ላይ በዝርዝር ከመግለጽ እቆጠባ
ለሁ ። ጊዜው ሲደርስ ግን ይገለፃል ። ሌላው ቀርቶ በሽምግልና መልክ
ጉዳዩን እናያለን ብለው የተንሸራተቱትን ጭምር ከመግለጽ እንደማልቆጠብ
በእርግጠኝነት እናገራለሁ ። ለምን እንዲህ ይደረጋል ? የትኞዎቹ ወላጆች
ናቸው እንዲህ ዓይነቱን ኢትዮጵያዊነት ያስተማሩን ? የትኞዎቹ ወላጆች
ናቸው ከፈሪሃ-እግዚአብሔር በዚህ መልክ እንድንሸሽ ያደረጉን ? ያሳዝናል!

ይህንንም ስል ሌሎች ማስረጃዎቼንና ልገልጻቸው የምፈልጋቸውን ነገ
ሁላችሁም በጠበቃ ተብዬው የምትደነቁበትን በተከታታይ ለማቅረብ ቃል
እገባለሁ ። በርግጥ ጊዜያችን ሽማግሌ የሌለበት ፣ በሃይማኖታችንም ሆነ
በባኅላችን የማንዳኝበት ወቅት ላይ ስለሆንን !! ጊዜ የሰጣቸው ሁሉ በመንግ
ሥትነት ስምና በተለያዩ ዘዴዎች ሀገርን አናውቅም ፣ የምንሠራው ቢዝነስ
ነው እያሉ የሕዝብን ሀብት የሚሞጨልፉበት ወቅት ላይ ነን !! ያም ቢሆን
ዓለማችን ጨርሶም ሕግ የላትም የምንልበት ደረጃ ላይ ስላልደረስን ባለችን
ጥቂት እንጥፍጣፊ ተስፋ ዕውነቱ በሕግ ፊት ገሃድ እንደሚሆን አምናለሁ።

ያልኋቸውን ሜዲያዎች ስም ለጊዜው ባልጠቅስም በኢሜል ብቻ ሳይሆን
በስልክም አነጋግረውኛል ። ለኔ የነገሩትን አንዱንም አልፈጸሙም ። ሕይ
ወት ከሰከንድ ተነስቶ ጊዜን እየለካ የደረሰበት እስኪደርስ ይጓዛል ። በሕይ
ወትም ውስጥ የተለያዩ ነገሮች ይከሰታሉ ! ኬዝዋን ያበለሻሸባት ጠበቃ ምን
ተፍረት በጎደለው ባኅሪው " ይህችን መታወቂያ የሌላትን ልጅ አስከስሳችሁ
ካገር ልታባርሯት ነው ? " እያለ ሲፎክር ብትሰሙ ምን ትላላችሁ ? ገንዘባ
ችን የሚበላው እኛ ነን ! የሚፎከርብን እኛ ነን ! እግዚአብሔር በሰውነትዋ
አውቆና ነፃነትን ሰጥቷት የፈጠራትን ኢትዮጵያዊት ልጅ በዓለም ላይ ጨር
ሶም እንደማትታወቅ አድርጎ አሁንም እየፎከረ ነው !!ጠበቃ ተብዬው በሚ
ዝናናበት ሀገር ላይ ያለችው ልጅስ ኑሮዋ ምን ይመስል ይሆን? በዚህ ጉዳይ
ስሜት ያልሰጣቸው ሜዲያዎች የአንድ ቀን ውሎ አዳር እንዴት ይገፋል
ብለው ይሆን የልጅቱን ጉዳይ ሕዝብ እንዳይሰማ እስካሁን በዝምታ የተመ
ለከቱት ። እጅግ አዝናለሁ ።

ስለዚህ በሕዝብ ስም የተመሠረታችሁ ሚዲያዎች ራሳችሁን ግልጽ ከማ
ድረግም ባሻገር ፤ በሕዝብ ብሶትና ምሬት ላይ አድልኦ ሳታደርጉ የደረሳች
ሁን ማንኛውንም ጽሁፍ ፤ ብሎም እናንተን የሚዘልፍ እንኳ ቢሆን ለአደባ
ባይ ማቅረብ እንዳለባችሁ በማሳሰብ :: ያንንስ ሃዘናችሁን የገለፃችሁበትን
ጉዳይ ለምንድነው ለአደባባይ ያላበቃችሁት ? እስቲ ምክንያቱን ግለጡልን
ያንንም ስል የጠበቃው ወገናዊነት የለንም ብላችሁ ማንነታችሁን ለትዝብት
እንዳታበቁ ከወዲሁ በጥንቃቄ እንድታስቡበት እጠቁማለሁ :: ምክንያቱም
ሌላ የሚወጣ ብዙ ጉድ ስላለ ነው :: ያ የተከበረውን ጠበቃችሁን በሀገራችን
ባኅልና ልማድ መሠረት ሽማግሌ ልከን እናውቀዋለን በሚሉ ሰዎች ሁሉ
ያላግባብ የወሰደውን ገንዘብ እንዲመልስልን ጠይቀነው ነበር ፤ ነገር ግን ከ3
ገጽ በልበለጠ ደብዳቤ ለዚያውም ልጁ ጽፋ የሰጠችውን ለኢሚግሬሽን አቅ
ርቦ 4086 ዶላር ወስዶ ኬዝዋን አሰናከለ ብለን ስንገልጽ ለምንድነው ጆሮ-
ዳባ ልበስ ብላችሁ በዝምታ የተዋጣችሁት ? መልሳችሁን ለመስማት እጓጓለ
ሁና የምትሉትን በሉ !!